በኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር
The Faderal Democratic Republic Of Ethiopia
Ministry of Federal Affairs

ቁጥር H1-816/001/03-84
Ref. No.
ቀን 24 ጥር 2003
Date

በዝርዝሩ ለተመለከቱት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- በ13ኛው የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ቀን በዓል ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር በተደረገ ውይይት የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦችና አርብቶ አደሮች ያስተላለፉትን የአቋም መግለጫ ስለማሳወቅ

አገር አቀፍ 13ኛው የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ቀን በዓል ጥር 17 እና ጥር 18/2003 ዓ.ም በደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል አስተናጋጅነት በጅንካ ከተማ በደማቅ ሁኔታ መከበሩ ይታወሳል።

በዚሁ በዓል ወቅት አርብቶ አደሮቹ ጥር 17 ቀን 2003 ዓ.ም ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ጋር ውይይት ያደረጉ ሲሆን የፌዴራልና የክልል መንግስታት ትኩረት ሰጥተው በመስራት ውጤት ማስመዝገብ በሚገቡ ጉዳዮች ዙሪያ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ አመራር ተሰጥቷል።

ከዚህ በተጨማሪ ጥር 18 ቀን 2003 ዓ.ም በበዓሉ ማጠቃለያ የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች የአቋም መግለጫ አውጥተዋል። በዚህ መሰረት የሚመለከተን የፌዴራልና የክልል አካላት በየዘርፉ ለተነሱ ጉዳዮች ትኩረት ሰጥተን የበኩላችንን ለመወጣት እንዲያስችል በውይይቱ በተነሱ ጉዳዮች መነሻ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተሰጡ አቅጣጫዎችን፣ እንዲሁም አቋም መግለጫውን 4 ገፅ አባሪ አድርገን የላክን መሆናችንን እየገለፅን የየድርሻችንን በመወጣት የአርብቶ አደሩን ህዝብ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚነት እንድናረጋግጥ እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር

ዶ/ር ሽፈራው ተክለማርያም
ሚኒስትር

ግልባጭ:-

- ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት - ከነአባሪው
- በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለአርብቶ አደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ - ከነአባሪው
- ለፓስቶራሊስት ፎረም ኢትዮጵያ - ከነአባሪው

**አዲስ አበባ**

- ለሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት ከነአባሪው
- ለተመጣጣኝ ልማት ዋና ዳሬክቶሬት ከነአባሪው
- ለሕዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት ከነአባሪው

**ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር**

PASTORALIST FORUM ETHIOPIA
RECEIVED STAMP
DATE 3/2/11
SIGNATURE

ስልክ Tel. 011-551 0000 ፋክስ Fax 011-551 1200 011-551 2639 የፖ.ሣ.ቁ. P.O.Box 5608 ኢ-ሜይል E-mail mofa@ethionet.et rass@ethionet.et አዲስ አበባ Addis Ababa

- **ለክቡር አቶ እስማኤል አሊሴሮ**
  የአፋር ብሔራዊ ክ/መንግስት ር/መስተዳድር
  **<u>ሰመራ</u>**
- **ለክቡር አቶ አብዲ መሃመድ**
  የሶማሌ ክልላዊ መንግስት ር/መስተዳድር
  **<u>ጅጅጋ</u>**
- **ለክቡር አቶ አለማየሁ አቶምሳ**
  የኦሮሚያ ብሔራዊ ክ/መንግስት ር/መስተዳድር
  **<u>ፊንፊኔ</u>**
- **ለክቡር አቶ ሽፈራው ሽጉጤ**
  የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክ/መንግስት ር/መስተዳድር
  **<u>ሀዋሳ</u>**
- **ለክቡር አቶ ተፈራ ደርበው**
  የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር
- **ለክቡር አቶ አለማየሁ ተገኑ**
  የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር
- **ለክቡር ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሐኖም**
  የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር
- **ለክቡር አቶ ደመቀ መኰንን**
  የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር
- **ለክቡር አቶ መኩሪያ ኃይሌ**
  የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር
- **ለክብርት ወ/ሮ ዘነቡ ታደሰ**
  የሴቶች፣ የሕፃናትና የወጣቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር
- **ለክቡር አቶ ድሪባ ኩማ**
  የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር
- **ለክቡር አቶ ደብረፂዮን ገ/መስቀል**
  የመገናኛና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር
- **ለክቡር ዶ/ር ተወልደ ብርሃን ገ/እግዚአብሔር**
  የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር
- **ለክቡር አቶ መላኩ ፈንታ**
  የኢትዮጵያ ገቢዎችና የጉሙሩክ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር
- **ለአቶ ሽፈራው አለሙ**
  የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
- **ለአቶ ምሕረት ደበበ**
  የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈፃሚ
- **ለአቶ አማረ አምሳሉ**
  የኢትየጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈፃሚ
- **ለአቶ ዛይድ ወ/ገብርኤል**
  የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ዋና ስራ አስፈፃሚ
  **<u>አዲስ አበባ</u>**

## ክቡር የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጥር 17/2003 በተከበረው 13ኛው የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ቀን በዓል ተሳታፊዎች ጋር ባደረጉት ውይይት በተነሱ ዋና ዋና ጉዳዮች የተሰጡ አቅጣጫዎች

ጥር 17/2003 በደቡብ ብ/ብ/ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በደቡብ ኦሞ ዞን ጅንካ ከተማ በተከበረው 13ኛው የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ቀን በዓል አርብቶ አደሮቹ ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጋር ውይይት አድርገዋል፡፡ በዚህ ውይይት ከተነሱ ጉዳዮች የፌዴራልና የክልል መንግስታት አስፈፃሚ አካላት ትኩረት ሰጥተው ውጤት እንዲያስመዘግቡና በሚቀጥለው ዓመት ሪፖርት እንዲያቀርቡ አመራር የተሰጠባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. **የእንስሳት ሀብት ልማትና ገበያ በተመለከተ፡-**

   ሀ. **የእንስሳት ምርትና ምርታማነት፡-**

   አርብቶ አደሩ ከእንስሳት ሀብቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን የተጀመሩ የኳራንታይንና የገበያ ማዕከላት ግንባታዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲጠናቀቁ፣ በየክልሉ የተጀመሩ የእንስሳት ህክምና ተቋማት የቅርብ ክትትል እየተደረገ ለአገልግሎት እንዲበቁ፣ አዳዲሶችም እንዲገነቡ፡፡ በተጨማሪም በእንስሳት ህክምና ተቋማት አካባቢ የሚታዩ የባለሙያና የመድሃኒት አቅርቦትና አጠቃቀም ችግሮች በቅርብ ክትትል እየተደረገባቸው እልባት እንዲሰጣቸው፣

   ለ. **የእንስሳት ገበያና የግብይት ስርዓት፡-**

   በየክልሉ የተጀመሩ የእንስሳት ገበያ ማዕከላት የመረጃ ስርዓት ይበልጥ እንዲጠናከሩ፣ ከአገር ውስጥና ከውጭም ገበያዎች ጋር በተሻለ ሁኔታ ትስስር እንዲፈጥሩና የአርብቶ አደሩ የህብረት ስራ ማህበራት አቅም በማሳደግ አርብቶ አደሩ እንስሳቱን በቀጥታ ለተጠቃሚው በማቅረብ ከምርቱ በላቀ ደረጃ ያለምንም ውጣ ውረድ መጠቀም የሚያስችል የተጠናከረ ድጋፍ በየደረጃው እንዲደረግ፣

2. **በአርብቶ አደሩ አካባቢ የመሬት አጠቃቀምን በተመለከተ፡-**

   በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚደረጉ የኢንቨስትመንት ስራዎች የአርብቶ አደሩን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ለግጦሽና ለእርሻ የሚሆን መሬት በየክልሉ በጥናት እንዲለይና በየደረጃው አርብቶ አደሩ በበቂ ደረጃ ውይይት እያደረገ ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችሉ ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲሰራ፣

3. **የተፋሰስ ልማትና የመንደር ማሰባሰብ ስራን በተመለከተ፡-**

   ሀ. በየክልሉ በህዝቡ ፈቃደኝነት ላይ ተመስርተው የተጀመሩ ውሃን ማዕከል ያደረጉ የልማትና በመንደር ማሰባሰብ ስራዎች ተጠቃሚ ከአርብቶ አደሩ ጋር በቂ ምክክር ተደርጎ በቂ የትምህርት፣ የጤና፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦትና የግብርና ኤክስቴንሽን ስርዓቱን በመዘርጋት ተጠቃሚነቱን በሚያረጋግጥ መልኩ ትኩረት ተሰጥቶ ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣

Records & Archives Section
Ministry of Federal Affairs

ለ. በአንዳንድ አርብቶ አደሩ ቀድሞ መሰባሰብ ለጀመረባቸው አካባቢዎች ቅድሚያ እየተሰጠና የከተማ ፕላን እየተሰራ ለሚገነቧቸው ቤቶች ዋስትና ሊያሰጥ በሚያስችል ቋሚ አሰራር እንዲታገዙ፣

4. **መጤ ዛፎችና አረም መከላከል በተመለከተ፡-**

በአርብቶ አደሩ አካባቢ የግጦሽ መሬቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ ያሉ መጤ ዛፎችና አረሞች በተለይ ‹‹ፕሮሶፒስጁሊፍሎራ›› በተመለከተ በየደረጃው የተጀመሩ ጥናቶችን በአፋጣኝ በማጠናቀቅ ህዝቡን ተጠቃሚ ሊያደርግ በሚያስችል ዘላቂ መፍትሄዎች ላይ በማተኮር ተግባራዊ እንዲሆን፣

5. **የውሃ ልማትን በተመለከተ፡-**

ሀ. በአርብቶ አደሩ አካባቢ የተጀመሩ የሰውና የእንስሳት መጠጥ ውሃ አቅርቦት ስራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ የአገልግሎት አሰጣጣቸው ላይ በቂ ክትትል እንዲደረግና የህዝቡ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ፣

ለ. እንደየክልሎቹ ተጨባጭ ሁኔታ የተጀመሩ ዘላቂ የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ጥናትና ግንባታ ስራዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው የቅርብ ክትትል እንዲደረግና ህብረተሰቡ በየደረጃው ተሳታፊና ተጠቃሚ በሚሆንበት አግባብ እንዲፈፀም፣

6. **የትምህርትና የጤና አገልግሎት በተመለከተ፡-**

ሀ. የትምህርት ሽፋን የማሳደግ ስራው ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ በተለይም ለትምህርት ጥራትና ለሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ፣

ለ. የጤና አገልግሎቱም በተመሳሳይ መንገድ ሽፋን ከማሳደግ ጐን ለጐን ህብረተሰቡ በተቋሞቹ በተሟላ መንገድ ተጠቃሚ እንዲሆን በሚያስችሉ የግብዓት አቅርቦት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ክትትል እንዲደረግ

7. **የመሰረተ ልማት ስራዎች (መንገድ፣ ቴሌ፣ መብራትና አውሮፕላን ማረፊያዎች)፡-**

ሀ. የመንገድ ልማት በተመለከተ በየክልሉ በፌዴራልም ሆነ በክልሎች የተጀመሩ የመንገድ ግንባታ ስራዎች እንዲጠናቀቁና ለአገልግሎት እንዲበቁ ለማስቻል በየደረጃው በቂ ትኩረት ተሰጥቶ ክትትል እንዲደረግ፡፡ በተጨማሪም በየክልል መንግስታቱ በኩል ወረዳን ከወረዳና ቀበሌን ከቀበሌ ለሚያገናኙ መንገዶች ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ፣

ለ. በአርብቶ አደሩ አካባቢ በፌዴራል መንግስት ለተጀመሩ የአውሮፕላን ማረፊያዎች (ጅንካ፣ ሰመራ፣ ጅጅጋ፣ ጐዴ)፣ የመብራትና የቴሌኮሙኒኬሽን ግንባታና አገልግሎት አቅርቦት ስራዎች የመንተት አዝማሚያ እያሳዩ ስለሆነ የቅርብ ክትትል እየተደረገባቸው እንዲጠናቀቁ፣ ለአገልግሎት ብቃትና ጥራታቸውም ትኩረት እንዲሰጥ፣

8. **የሰላምና ፀጥታ በተመለከተ**

በአርብቶ አደሩ አካባቢዎች በክልል ውስጥም ሆነ ከአጐራባቾች የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት በመንግስት አካላት የሚደረጉ ጥረቶች እንደተጠበቁ ሆነው በቅድሚያ በየአካባቢው ባሉ የህዝቡ ባህላዊ አደረጃጀቶች እንዲፈቱ በየደረጃው የሚገኘው የመንግስት አካላት እንዲያበረታቱና ድጋፍ እንዲሰጡ፣

Records & Archives Section
Ministry of Federal Affairs

ለ. በአንዳንድ አርብቶ አደሩ ቀድሞ መሰባሰብ ለጀመረባቸው አካባቢዎች ቅድሚያ እየተሰጠና የከተማ ፕላን እየተሰራ ለሚገነቧቸው ቤቶች ዋስትና ሊያሰጥ በሚያስችል ቋሚ አሰራር እንዲታገዙ፣

4. **መጤ ዛፎችና አረም መከላከል በተመለከተ፡-**

በአርብቶ አደሩ አካባቢ የግጦሽ መሬቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ ያሉ መጤ ዛፎችና አረሞች በተለይ ‹‹ፕሮሶፒስጁሊፍሎራ›› በተመለከተ  በየደረጃው የተጀመሩ ጥናቶችን በአፋጣኝ በማጠናቀቅ ህዝቡን ተጠቃሚ ሊያደርግ በሚያስችል ዘላቂ መፍትሄዎች ላይ በማተኮር ተግባራዊ እንዲሆን፣

5. **የውሃ ልማትን በተመለከተ፡-**

ሀ. በአርብቶ አደሩ አካባቢ የተጀመሩ የሰውና የእንስሳት መጠጥ ውሃ አቅርቦት ስራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ የአገልግሎት አሰጣጣቸው ላይ በቂ ክትትል እንዲደረግና የህዝቡ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ፣

ለ. እንደየክልሎቹ ተጨባጭ ሁኔታ የተጀመሩ ዘላቂ የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ጥናትና ግንባታ ስራዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው የቅርብ ክትትል እንዲደረግና ህብረተሰቡ በየደረጃው ተሳታፊና ተጠቃሚ በሚሆንበት አግባብ እንዲፈፀም፣

6. **የትምህርትና የጤና አገልግሎት በተመለከተ፡-**

ሀ. የትምህርት ሽፋን የማሳደግ ስራው ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ በተለይም ለትምህርት ጥራትና ለሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ፣

ለ. የጤና አገልግሎቱም በተመሳሳይ መንገድ ሽፋን ከማሳደግ ጐን ለጐን ህብረተሰቡ በተቋሞቹ በተሟላ መንገድ ተጠቃሚ እንዲሆን በሚያስችሉ የግብዓት አቅርቦት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ክትትል እንዲደረግ

7. **የመሰረተ ልማት ስራዎች (መንገድ፣ ቴሌ፣ መብራትና አውሮፕላን ማረፊያዎች)፡-**

ሀ. የመንገድ ልማት በተመለከተ በየክልሉ በፌዴራልም ሆነ በክልሎች የተጀመሩ የመንገድ ግንባታ ስራዎች እንዲጠናቀቁና ለአገልግሎት እንዲበቁ ለማስቻል በየደረጃው በቂ ትኩረት ተሰጥቶ ክትትል እንዲደረግ። በተጨማሪም በየክልል መንግስታቱ በኩል ወረዳን ከወረዳና ቀበሌን ከቀበሌ ለሚያገናኙ መንገዶች ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ፣

ለ. በአርብቶ አደሩ አካባቢ በፌዴራል መንግስት ለተጀመሩ የአውሮፕላን ማረፊያዎች (ጅንካ፣ ሰመራ፣ ጅጅጋ፣ ጐዴ)፣ የመብራትና የቴሌኮሙኒኬሽን  ግንባታና አገልግሎት አቅርቦት ስራዎች የመንተት አዝማሚያ እያሳዩ ስለሆነ የቅርብ ክትትል እየተደረገባቸው እንዲጠናቀቁ፣ ለአገልግሎት ብቃትና ጥራታቸውም ትኩረት እንዲሰጥ፣

8. **የሰላምና ፀጥታ በተመለከተ**

በአርብቶ አደሩ አካባቢዎች በክልል ውስጥም ሆነ ከአጐራባቾች የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት በመንግስት አካላት የሚደረጉ ጥረቶች እንደተጠበቁ ሆነው በቅድሚያ በአካባቢው ባሉ የህዝቡ ባህላዊ አደረጃጀቶች እንዲፈቱ በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላት እንዲያበረታቱና ድጋፍ እንዲሰጡ፣

Records & Archives Section
Ministry of Federal Affairs

8. የአጐራባች ክልሎች ትብብር ለአርብቶ አደሩ ዘላቂ ልማትና ሰላም ወሳኝ በመሆኑ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንጠይቃለን፡፡
9. የአርብቶ አደሩ ጉዳዮች አካባቢያዊና ድንበር ተሻጋሪ እንደመሆናቸው መጠን ከጐረቤት አገሮች ጋር በሰላምና በልማት ጉዳዮች በጋራ የመስራቱ ሂደት ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንጠይቃለን፡፡
10. በአርብቶ አደር አካባቢ የትምህርት እና የጤና አገልግሎት የአርብቶ አደሩን አኗኗር ባማከለ መልኩ በስፋት እና በጥራት ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንጠይቃለን፡፡

በመጨረሻም 13ኛው የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ቀን በዓል በድምቀት እንዲከበር ላደረጉት ለደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልላዊ መንግስት፣ ለደቡብ ኦሞ ዞን መስተዳደርና ህዝብ፣ ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለአርብቶ አደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና ለፓስቶራሊት ፎረም ኢትዮጵያ የላቀ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

***‹‹በአርብቶ አደሩ አካባቢ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በመተግበር የኢትዮጵያን ህዳሴ የማይቀለበስበት ደረጃ ላይ እናደርሳለን››***

ጥር 18/2003 ዓ.ም

ጂንካ

የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር
የሪኮርድና ማህደር ክፍል
Records & Archives Section
Ministry of Federal Affairs